**Government of the District of Columbia**
Department of Employment Services

MURIEL BOWSER
ከንቲባ

ዶ/ር UNIQUE MORRIS-HUGHES
ዳይሬክተር

**የአዳዲስ ደንቦች ማስታወቅያ**

**የ D.C. Act 21-485 (Act)፣ የ2016 የBuilding Service Employees Minimum Work Week Act of 2016 በመባልም ይታወቃል**

**በዚህ ህግ መሰረት ሽፋን ያላቸዉ ሰራተኞች ቢያንስ ለ30 ሰአታት ዝቅተኛዉን የስራ ሳምንት እንዲሰሩ መርሃግብር ተይዞላቸዋል።**

---

**ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች**

- ሽፋን ያለዉ ሰራተኛ ማለት የተሸፈነዉን ቦታ ወይም የንግድ ቦታ ለመጠገን፣ ንፅህና እና አጠቃላይ ጥራትን ለመጠበቅ በተሸፈነ ቦታ ዉስጥ ወይም አካባቢ የንፅህና አገልግሎትን፣ የህንፃ ጥገና አገልግሎትን ወይም ሌሎች አገልግሎት የሚያከናዉን ነዉ።

**የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ**

- ሽፋን ያለዉ ሰራተኛ ሽፋን ያለዉ አረፍት በሚወስድበት ግዜ አረፍቱ በትንሹ የ30 ሰዓት የስራ ሳምንት ዉስጥ ይቆጠራል፤ በእያንዳንዱ ሽፋን ባለዉ ቦታ በፅዳት አገልግሎት ላይ ለተሰማሩ ሽፋን ያላቸዉ ሰራተኞች የሆኑ እስከ 20% የሚሆኑ የስራ ሰዓታት ሽፋን ላላቸዉ የትርፍ ገዜ ሰራተኞች ቢያንስ 4 ሰዓት በምሽት ፈረቃ እና በሳምንት 20 ሰዓት በድምሩ እስከ 10 የትርፍ ሰዓት የስራ መደቦች በአንድ ሽፋን ያለዉ ቦታ ሊቆይ ይችላል።

**የመለጠፍ መስፈርቶች**

- ሽፋን ያለዉ አሰሪ ማስታወቂያዉን በግልፅ ቦታ መለጠፍ እና ማስጠበቅ አለበት ይህም በከንቲባዉ ተወስኖ ለእያንዳንዱ ሽፋን ያለዉ አሰሪ የዚህን ህግ አግባብነት ያላቸዉን ድንጋጌዎች ቅንጭብጭብ ወይም ማጠቃለያ እና ቅሬታ ስለማቅረብ መረጃን ያካተተ ህግ መስጠት አለበት።
- ከጁን 19፣ 2004 ጀምሮ በ2004 የቋንቋ ተደራሽነት ህግ ክፍል 2 (D.C. Law 15-167;D.C. Official Code g 2-t931) ላይ እንደተገለፀዉ ሽፋን ያለዉ አሰሪ በዚህ ህግ መለጠፍ የሚያስፈልገዉን ማስታወቂያ በእንግሊዘኛ እና የተገደበ ወይም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ በሌላቸዉ ሽፋን ያላቸዉ ሰራተኞች በሚነገሩ ሁሉም ቋንቋዎች መለጠፍ አለበት። (ለ) በዚህ ክፍል የተቀመጡትን የመለጠፍ መስፈርቶች ያላሟላ ሽፋን ያለዉ አሰሪ ለተቀመጠዉ ቅጣት ተገዢ ይሆናል። (ለቅጣቶች የህጉን ክፍል 8 ይመልከቱ)

**ቅጣቶች**

- በአንቀፅ 5 ያሉትን የመለጠፍ መስፈርቶች ሆን ብሎ የጣሰ ሽፋን ያለዉ አሰሪ ማስታወቂያዉን መለጠፍ ካልቻለ አጠቃላይ ቅጣቱ ከ$500 የማይበልጥ ለእያንዳንዱ ቀን ከ$100 የማይበልጥ የፍትሐ ብሄር ቅጣት መገመት አለበት።
- ከመለጠፍ መስፈርቶቹ ዉጪ የዚህን ህግ ማናቸዉንም መስፈርቶች ያላሟላ ሽፋን ያለዉ አሰሪ ጥሰቱ በቀጠለበት ለእያንዳንዱ ጥሰት $5,000 የማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል። ለመጀመርያዉ ጥሰት (ሀ) ከፍተኛ እስከ $500 የሚደርስ ቅጣት እና (ለ) ለማንኛዉም ተከታይ ጥሰት ከፍተኛዉ እስከ $1,000 የሚደርስ ቅጣት ይቀጣል።

**የ2016 የግንባታ አገልግሎት ሰራተኞች አነስተኛ የስራ ሳምንት ሕግ ሙሉ ፅሑፍ ለማግኘት ወደ D.C.Act 21-485 ይሂዱ።**

**ማንኛዉም ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ:- የቅጥር አገልግሎቶች መምርያ፣ የክፍያ ሰዓት ቢሮ፣ 4058 Minnesota Avenue, SE, Suite 3600, Washington, D.C. 20019, (202) 671-1880 ን ያነጋግሩ ወይም ይጎብኙ።**